# የተሻሻለውን የቤተሰብ ሕግ ለማሻሻል የቀረበው ረቂቅ

# አዋጅ አጭር መግለጫ

የኢፌዴሪ የሚኒስትሮች ም/ቤት ሚያዚያ 17 ቀን 2009 ዓ.ም ባደረገው 28 መደበኛ ስብሰባው ብሔራዊ የህጻናት ፖሊሲን ያፀደቀ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ፖሊሲው ወላጆቻቸውን በተለያዩ ምክንያቶች ያጡና በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ የሚገኙ ህፃናት በኢትዮጵያ ባህል፣ በተወለዱበት አካባቢ ወግ፣ ልማድና ማህበረሰባዊ እሴት ታንፀው እንዲያድጉ በአገር ውስጥ ባሉ አማራጭ የድጋፍና እንክብካቤ አገልግሎቶች ማለትም በማህበረሰብ አቀፍ ድጋፍና እንክብካቤ፣ በሀገር ውስጥ ጉዲፈቻ፣ በአደራ ቤተሰብ እና በመልሶ ማቀላቀልና ማዋሀድ ፕሮግራሞች ብቻ እንዲደገፉ ማድረግ የፖሊሲው አንዱ ዓላማ ሆኖ ተቀምጧል፡፡

በተመሳሳይ ሁኔታ የፖሊሲው ዋና ዋና ጉዳዮች ተብለው ከተጠቀሱት መካከል በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ የሚገኙ ሕፃናት የሚደገፉበት ሁኔታ አንዱ ነው፡፡ በዚሁ መሰረት ወላጆቻቸውን በተለያዩ ምክንያቶች ያጡና ተንከባካቢ የሌላቸው ሕጻናት የቤተሰብ ፍቅር፣ ክብካቤና ጥበቃ አግኝተውና መሠረታዊ ፍላጎታቸው ተሟልቶ እንዲያድጉ ለማድረግ የሚያስችሉ የሀገር ውስጥ ጉዲፈቻ፣ የአደራ ቤተሰብና የማህበረሰብ አቀፍ የድጋፍና እንክብካቤ ፕሮግራሞችን ማስፋፋት፣ ለሕይወታቸው ጠቃሚ የሆኑ የምክር አገልግሎት ሰጪ ተቋማት እንዲስፋፉና ተደራሽ እንዲሆኑ ማድረግ፣ ኢኮኖሚያዊና ማሕበራዊ አገልግሎቶችን በጥራት፣ በስፋትና በወቅቱ የሚያገኙበትን ሁኔታ ማመቻቸት፣ እንደየ ችግራቸው ዓይነት በማህበረሰቡ ያሉ እሴቶችን በመቀመርና በማስፋፋት በሀገር ውስጥ ባሉ አማራጭ የድጋፍና እንክብካቤ ዘዴዎች ብቻ እንዲደገፉ እና ይህንንም አሰራር በተገቢው ሁኔታ መጠናከር እንዳለበት ያመለክታል፡፡

በሌላም በኩል ተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 193 እና 194(3)(መ) እና (4) ላይ ወላጆቻቸውን በተለያዩ ምክንያቶች ያጡና በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ የሚገኙ ህፃናት ድጋፍ ከሚያገኙበት የአገልግሎት አይነቶች ውስጥ የውጭ ሀገር ጉዲፈቻ እንደመጨረሻ የሚሰወድ እርምጃዎች እንደሆነ ተመልክቷል፡፡ የውጭ ሀገር ጉዲፈቻ የተፈጥሮ ቤተሰብ ፍቅርና እንክብካቤ ሙሉ በሙሉ የማይተካ ከመሆኑም በላይ የዚህ አማራጭ ተጠቃሚ የሆኑ ህጻናት በማይውቁት ቋንቋ፣ ባህልና ሃገር እንዲያድጉ በመደረጋቸው ለማንነት

ቀውስ፣ ለስነ-ልቦናዊና ማህበራዊ ችግሮች ሲጋለጡ በመታየታቸው በአሁኑ ጊዜ ተመራጭ የድጋፍና እንክብካቤ ዘዴ ሆኖ እንዳልተገኘ ፖሊው ያመለክታል።

በመሆኑም መንግስት ባወጣው ብሔራዊ የህጻናት ፖሊሲ እና በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ መካከል የሚቃረኑ ሀሳቦች በመኖራቸው ሁለቱ ሰነዶች ተጣጥመው እንዲሄዱ ለማድረግ የውጭ ሀገር ጉዲፈቻን የሚመለከቱትን የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አንቀጾች እንዲሰረዙ በማድረግ ህጉ እንዲሻሻል ተደርጓል። በተጨማሪም ፖሊሲው ከመውጣቱ በፊት እና ከወጣም በኋላ በነባሩ የቤተሰብ ህግ መሰረት ጉዳያቸው በፍ/ቤት እየታዩ ያሉ ጉዳዮች በምን መልኩ መጠናቀቅ አለባቸው የሚለውን ጥያቄ የማሻሻያ ህጉ መልስ ሊሰጠው የሚገባ በመሆኑ ይህ የማሻሻያ አዋጅ ከመጽናቱ በፊት በፍርድ ቤት የተጀመሩ የውጭ ሃገር የጉዲፈቻ ጉዳዮች በነባሩ የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 መሰረት ውሳኔ እንደሚያገኙ በረቂቅ ማሻሻያ ህጉ ላይ ተመልክቷል።